**SchooLinks – የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ከዚያ በላይ እቅድ (ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል)**

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ፣አዲሱን የዋሽንግተን ስቴት  የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ከዚያ በላይ እቅድ (High School and Beyond Plan - HSBP) መድረክ የሆነውን SchooLinks በይፋ አስተውውቋል። ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የወደፊት ዕቅዳቸውን (HSBP) ለማጠናቀቅ SchooLinks ይጠቀማሉ።ይህ ዕቅድ ተማሪዎች ፍላጎቶቻቸውን እንዲመረምሩ፣ግቦችን እንዲያወጡ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ለሚኖራቸው ሕይወት እንዲያቅዱ የሚረዳ የዋሽንግተን ስቴት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ (የምረቃ) መስፈርት ነው።

**ቤተሰቦች ማወቅ የሚገባቸው ነገሮች:**

- ተማሪዎች መድረኩን መጠቀም (መግባት) የሚጀምሩት መስከረም 2, 2026 ነው።
- SchooLinks የዲስትሪክቱ የኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት መድረክ የሆነውን Naviancን ተክቷል።
- ተማሪዎች የሙያ መስኮችን፣ኮሌጆችን፣የስራ ልምምድ (apprenticeships) ፕሮግራሞችን፣ የማሰልጠኛ መርሃ-ግብሮችን እና ሌሎች ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የሚከተሏቸውን መንገዶች ለማሰስ SchooLinks መጠቀም ይችላሉ።
- ተማሪዎች በየዓመቱ የሁለተኛ ደረጃ  ትምህርት እና የወደፊት ዕቅዳቸውን (High School and Beyond Plan) የሚያድሱ ሲሆን፣ወደ ትምህርታዊ እና ሙያዊ ግቦቻቸው እያደረጉት ያለውን እድገትም ይከታተላሉ።
- ተማሪዎች  የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መለያቸውን( account) በመጠቀም በ Clever በኩል ወደ SchooLinks መግባት ይችላሉ።ተማሪዎች እንዴት መግባት እንደሚችሉ መመሪያ ለማግኘት Clever Student Portal ይጎብኙ።
- ተማሪዎች መድረኩን መጠቀም ከጀመሩ በኋላ፣ወላጆች/አሳዳጊዎች የወላጅ መለያ(account)እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ የሚገልጽ መረጃ ይደርሳቸዋል።
- የወላጅ/አሳዳጊ መለያ(account) ቤተሰቦች የተማሪዎቻቸውን የHSBP እድገት እንዲመለከቱ እና የኮሌጅ እና የሙያ አማራጮችን አብረው እንዲያስሱ ያስችላቸዋል።
- ተማሪዎች በትምህርት ዓመቱ በሙሉ በክፍል ውስጥ በሚሰጡ ትምህርቶች፣በየትምህርት ቤት አማካሪዎች እና በየኢንተርኔት (online) ግብዓቶች አማካኝነት ድጋፍ ይደረግላቸዋል።
- ተጨማሪ መረጃዎች፣መመሪያዎች እና በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች (FAQs) በ SchooLinks webpage ላይ ይገኛሉ።

ጥያቄ አለዎት? የትምህርት ቤትዎን የአማካሪ ቡድን (Counseling Team) ያነጋግሩ ወይም በ CCR@seattleschools.org ኢሜይል ያድርጉ።